**ላይፍ ላይን**

- በስልኮ ወይም ኢንተርኔት አገልግሎት ላይ እስከ 9.25 የአሜሪካ ዶላር ቅናሽ ያግኙ
- ላይፍ ላይን የእርስዎን የስልክ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ወርሃዊ ወጪ ለመቀነስ የሚሰራ የፌዴራል ፕሮግራም ነው።

**ግለሰቦች ያላቸው ተገቢነት**

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የመንግስት የጥቅማ ጥቅም ፕሮግራሞች መካከል **በአንደኛው** ላይ ተሳታፊ ከሆኑ ወይም ደግሞ በፌዴራል የድህነት መመሪያዎች መሰረት ገቢዎ 135% ከዚያ በታች ከሆነ ይህንን ቅናሽ ለማግኘት ተገቢነት አለዎት።

- የተጨማሪ ምጣኔ ምግብ (Nutrition) ድጋፍ ፕሮግራም (ኤስ.ኤን.ኤፒ)
- ሜዲክኤይድ
- የፌዴራል የህዝብ ቤቶች ድጋፍ (ኤፍ.ፒ.ኤች.ኤ)
- የአባት/እናት ጡረተኞች የጡረታ እና መቋቋሚያ ጥቅማ ጥቅም
- ተጨማሪ የዋስትና ገቢ (ኤስ.ኤስ.አይ)

**ቤተሰቦች ያላቸው ተገቢነት**

ቤተሰብ ማለት ገቢ እና ወጪ የሚጋሩ ሰዎች የሚገኙበት ቡድን ማለተ ነው።

- በአንድ ቤተሰብ ለማግኘት የሚፈቀድልዎት አንድ የላይፍላይን ቅናሽ ብቻ ነው።
- አንድ ቤት ውስጥ ተጋርተው የሚኖሩ ከሆነ በ LifelineSupport.org. ላይ የሚገኘውን የቤተሰብ (Household Worksheet) ይሙሉ። ከዚህ በተጨማሪ የእርስዎን የላይፍላይን አገልግሎት አቅራቢ መጠየቅ ይችላሉ።

**ማመልከቻ ማቅረብ የሚቻልባቸው ሶስት መንገዶች**

1. በኦንላይን ያመልክቱ

    ሀ) የኦንላይን ማመልከቻውን ከ nv.fcc.gov/lifeline ላይ ያግኙ

2. ማመልከቻዎን ይላኩ

    ሀ) ከ LifelineSupport.org. ላይ የማመልከቻ ቅጽ ፕሪንት ያድርጉ

ለ) ቅጹን ይሙሉ እና ከተገቢነት ማረጋገጫ ጋር በሚከተለው አድራሻ ይላኩት-

ላይፍላይን ሰፖርት ሴንተር

መ.ሣ.ቁ. 7081

ለንደን፤ ኬ.ዋይ 40742

3. ከስልክ ወይም ኢንተርኔት ኩባንያ ጋር ግንኙነት ይፍጠሩ

U) በ LifelineSupport.org. አማካኝነት ላይፍ ላይን የሚያቀርብ ድርጅት ያግኙ

ለ) Near Me የሚሉትን ኩባንያዎች ክሊክ ያድርጉ

ካሊፎርኒያ ውስጥ (CaliforniaLifeline.come) ኦሪገን ውስጥ (Lifeline.Oregon.gov) ወይም ቴክሳስ ውስጥ (TexasLifeline.org) የሚኖሩ ከሆነ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ለማወቅ የግዛትዎን ድረ-ገጽ ይመልከቱ።

## እርስዎ ተገቢ ስለመሆንዎ እንዴት ማሳየት ይችላሉ

- በሚከተሉት መንገዶች ለላይፍ ላይን ተገቢነት ያለዎ ስለመሆንዎ ማረጋገጫ ማሳየት ሊያስፈልግዎ ይችላል፡-
    - የእርስዎ ኤስ.ኤን.ኤ.ፒ ወይም ፕሮግራም ደብዳቤ ቅጂ
    - በፌዴራል የድህነት መመሪያዎች መሰረት ገቢዎ 135% ወይም ከዚያ በታች መሆኑን ለማረጋገጥ የክፍያ ሰነድ ወይም የታክስ ተመላሽ ቅጂ

*በትራይባል ላንድስ የሚኖሩ ከሆነ አገልግሎትዎን በተመለከተ ተጨማሪ ቅናሽ ሊያገኙ ይችላሉ።

የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ እና ማመልከቻዎን ለማቅረብ ድጋፍ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ከላይፍ ላይን የድጋፍ ማዕከል ጋር ግንኙነት ይፍጠሩ፡-

(800) 234-9473

9ኤ.ኤም- 9ፒ.ኤም ኢቲ

በሳምንት 7 ቀናት

LifelineSupport@usac.org

www.LifelineSupport.org

ላይፍላይን የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ተገቢነቱ ላላቸው ሸማቾች በተሻለ ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ የሚሰራ የፌዴራል ኮሙኒኬሽንስ ኮሚሽን (ኤፍ.ሲ.ሲ) ፕሮግራም ነው። ዩኒቨርሳል ሰርቪስ አድሚኒስትሬቲቭ ካምፓኒ (ዩ.ኤስ.ኤ.ሲ) የላይፍ ላይን ፕሮግራሞችን ያስተዳድራል። ዩ.ኤስ.ኤ.ሲ እርስዎ ለፕሮግራሙ እንዲያመለክቱ፣ የተገቢነት መስፈርቶችን እንዲገነዘቡ እና በአመታዊ የማስተካከያ ሂደቶች አማካኝነት ጥቅሞችዎ ወቅታዊ እንዲሆኑ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።